Tel/Fax: 703-379-0805

MOA AMBESSA
P.O. Box 2808
Arlington, VA 22202

የኢትዮጵያ የዘውድ ምክር ቤት
THE CROWN COUNCIL OF ETHIOPIA

በልዑል በከረ ፍቅረሥላሴ የኢትዮጵያ ዘውድ እንደራሴ

እና

በልዑል ኤርምያስ ሣህለሥላሴ የዘውድ ምክር ቤት ሰብሳቢ

የተሰጠ መግለጫ

ግንቦት ፲ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ/ም

ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ አምሐሥላሴ ከገናናው አባታቸው ከአፄ ኃይለሥላሴ የወረሱትን ለኢትዮጵያ ዘውድ ኃላፊነታቸውና በሕዝብ የተጣለባቸውን ታላቅ አደራ በሚገባ ለመወጣት ሲሉ ከዘውድ ምክር ቤት አባላት ጋር በሰፊው ከመከሩ በኋላ፣ እኛን ስማችን ከላይ የተጠቀስነውና የተቀሩትንም የንጉሣዊ ቤተሰብ አባላትን መርጠው መሾማቸው ከዚህ ቀደም በዜና ማሰራጫዎች ለሕዝብ ተገልጿል።

እኔና ወንድሜ ልዑል ኤርምያስም እንደ ስርዓቱ ሹማቸውን ስመን ሐላፊነቱን ፈቅደን መቀበላችንን በደስታ እስታውቀናል።

ይህንን ከባድ ኃላፊነት የተቀበልንበት ዋናው ምክንያት ዘመናዊ የዘውድ አመራር ለአገር ክብረትና ዕድገት ይጠቅማል ብሎ ለሚያምነው የኢትዮጵያ ሕዝብ አለኝታ ለመሆንና የዘውድ ባለአደራ የነበሩት አባታችን አፄ አምሐሥላሴ ለብዙ ዘመናት የቆየውን የዘውድ ቅርሳችንን ለእኛ ለተተኪው ትውልድ በአስተማማኝ ሁኔታ ለማስተላለፍ የነበራቸውን ጥብቅ ፍላጎት በመመልከት ነው። ይህንንም ለማድረግ ግርማዊነታቸው ውድ